2

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር ተ/ህ/ሕ/5/507
Ref. No
ቀን
Date

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣ
<u>አዲስ አበባ</u>

በተወሰኑ የጠረፍ አካባቢዎች በምግብ ሸቀጦች እና በባህላዊ አልባሳት አቅርቦት ረገድ የሚታየውን ችግር ለማቃለል በእነዚህ አካባቢዎች ለሚኖረው ሕዝብ የሚቀርቡ ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር የሚታይባቸው የምግብ ዓይነቶች እና ባህላዊ አልባሳት በፍራንኮ ቫሉታ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ማድረግ የሚያስችል መመሪያ ወጥቷል።

ስለዚህ መመሪያውን ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ ከህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>

- ለንግድ ሚኒስቴር
- ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
  <u>አዲስ አበባ</u>

- ለሱማሌ ብ/ክ/መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
- ለአፋር ብ/ክ/መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
- ለኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

Lett.W/GT

ስልክ
TEL 251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 01, 63 86 39
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905, 1037
ፋክስ
FAX. 251-11-155 13 55, 55 14 96
251-11-155 39 44
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Addis Ababa - Ethiopia

# በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጐች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮ ቫሎታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለመፍቀድ የወጣ መመሪያ ቁጥር 40/2007

የጠፊር አካባቢዎች የመሠረተ ልማት አውታሮች በበቂ ሁኔታ ያልተዘረጋባቸው በመሆኑ በእነዚህ አካባቢዎች ነዋሪ የሆነው ሕዝብ በአገር ውስጥ የሚመረቱ የምግብ አቅርቦቶችን እና አልባሳትን በቀላሉ ማግኘት የማይችል በመሆኑ፣

በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብ በሕገ-ወጥ መንገድ ወደአገር በሚገቡ ምርቶች በመጠቀም ከሚደርስበት የጤና ችግር እና እንዲከፍል ከሚገደደው ያልተመጣጠነ ዋጋ መታደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፡

በጠረፍ አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ ሕጋዊ የሆነውን የገቢና የወጪ ንግድ አሠራር እንዲከተል ማድረግ ሕጋዊ የሆነውን የንግድ ሥርዓት የሚያጐለብት በመሆኑ፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጁ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአንዳንድ የጠፊር አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጐች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮ ቫሎታ) ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የወጣ መመሪያ ቁጥር " 40/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው ከመመሪያው ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከቱት ቦታዎች ነዋሪ ለሆኑ ዜጐች ለሚቀርቡ ምግብና ባህላዊ አልባሳት ብቻ ነው፡፡

## 3. በፍራንኮ ቫሎታ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው የሚገቡ ምግቦችና ባህላዊ አልባሳት

በዚህ መመሪያ መሠረት በፍራንኮ ቫሎታ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር ሊገቡ የሚችሉት ከመመሪያው ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ የተዘረዘሩት ምግቦችና ባህላዊ አልባሳት ብቻ ናቸው፡፡

## ያለውጭ ምንዛሬ ክፍያ (በፍራንኮ ቫሉታ) ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚችሉ ነጋዴዎች

በዚህ መመሪያ መሠረት በፍራንኮ ቫሎታ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎችን ሊያስመጡ የሚችሉት ከንግድ ሚኒስቴር የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው እና በየክልሉ መንግስታት ለእያንዳንዱ አካባቢ ለምግብና ለባህላዊ አልባሳት በአቅራቢነት የሚመረጡ ሶስት ህ/ሥ/ማህበራት ወይም ነጋዴዎች ይሆናሉ፡፡

5. **በፍራንክቫሉታ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ አቅርቦቶች ዓይነትና መጠን**

1. የኦሮሚያ፣ የአፋር እና የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የንግድ ቢሮዎች ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ በተዘረዘሩት አካባቢዎች የሚኖሩትን ሕዝቦች ብዛት፣ የምግብ ፍላጐት እና የባህላዊ አልባሳት መጠን እንዲሁም በተለይ በየክልሎቹ/ከተማ ከሚያስፈልገው ምግብ ውስጥ በእርዳታ ወደ ክልሎቹ/ከተማ የሚገባውን ምግብ መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፈቃድ ከተሰጣቸው በእያንዳንዱ አቅራቢ ከእያንዳንዱ የምግብ ዓይነት እና ከተፈቀደው ባህላዊ አልባሳት ወደ አገር የሚገባውን መጠን ይወስናሉ፣

2. የየክልሉ የንግድ ቢሮዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ-1 መሠረት የሰጡትን ውሳኔ በየክልላቸው ለሚገኙ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች ያሳውቃሉ፣

6. **ክልከላና ገደብ**

1. በዚህ መመሪያ በተጠቀሱት ክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች ለሚገኙ ነዋሪዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ በፍራንክቫሉታ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር የገቡ ምግብና ባህላዊ አልባሳቶች በማናቸውም ሁኔታ ከተፈቀደላቸው አካባቢዎች ውጪ በክልሉም ይሁን በሌላ የአገሪቱ ክፍል ማስተላለፍና ለተለየ ጥቅም ማዋል የተከለከለ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ-1 የተደረገውን ገደብ በመተላለፍ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ከተፈቀደበት አካባቢ ውጭ ለገበያ ሲቀርብ ወይም ጥቅም ላይ ሲውል የተገኘ የምግብ እና ባህላዊ አልባሳት ላይ በየክልሉ የሚገኙ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፣

3. ወደ እያንዳንዱ ክልል የሚገቡ ሸቀጦች አቅራቢያቸው ካሉት ወደቦች በመነሳት ወደ ክልሉ የሚወስደውን የትራንስፖርት መስመር በመጠቀም የተጠቀሱትን ዕቃዎች ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከእነዚህ መስመሮች ውጪ በሌላ አቅጣጫ ሸቀጦቹን ማጓጓዝ አይቻልም፡፡

## 7. የመቆጣጠር ኃላፊነት

1. የሞያሌ ወረዳ፣ የቦረና ዞን፣ የአፋር እና የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በፍራንኮ ቫሉታ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ የገባው የምግብና ያባህል አልባሳት በዚህ መመሪያ ለተፈቀደላቸው ነዋሪዎች ብቻ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት የመዘርጋት እና ከተፈቀደበት አካባቢ ውጪ ለገበያ እንዳይቀርብ እና ጥቅም ላይ እንዳይውል ጥብቅ ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

2. በየክልሎቹ ያሉ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ በፍራንኮ ቫሎታ የገባው የምግብ እና የባህል አልባሳት ዓይነትና ብዛት ተገቢው የጉምሩክ ቁጥጥርና ሥነ-ሥርዓት እየተፈፀመበት ወደተፈቀደው አካባቢ እንዲገባ የማድረግና በህገ-ወጥ መንገድ ሲዘዋወር በተገኘው ላይ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ እንዲሁም ከየክልሉ ንግድ ቢሮዎች በሚቀርብለት ማረጋገጫ መሠረት ለቀጣይ ኦፕሬሽን ፈቃድ መስጠት አለበት፡፡

3. የየክልሉ ንግድ ቢሮዎች ቀደም ሲል አስመጪዎች ያስገቡት የምግብ እና ባህላዊ አልባሳት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በማረጋገጥ ለቀጣይ ኦፕሬሽን ዲክላራሲዮን መክፈት እንዲችሉ በክልላቸው ለሚገኙ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች ማረጋገጫ መስጠት አለባቸው፡፡

4. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋናው መ/ቤት የየክልሎቹን መንግሥታት የንግድ ቢሮዎችና በየክልሎቹ የሚገኙ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች በተገቢው ሁኔታ እየሰሩ መሆኑን በዓመት ሁለት ጊዜ ለመከታተል የሚያስችለውን የክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## 8. መብቱን ስለማቋረጥ

በዚህ መመሪያ የተፈቀደው ልዩ መብት ለሕዝቡ የተፈለገውን ጥቅም ያላስገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ በማናቸውም ጊዜ እንዲቋረጥ ሊወሰን ይችላል፡፡

9. ***የተሻረ መመሪያ***

ለሱማሌ ክልል ሕዝብ የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮ ቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የወጣው መመሪያ ቁጥር 28/2002 ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ ተሽሯል፡፡

10. ***መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን***

ይህ መመሪያ ከህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥቅምት 13 ቀን 2007 ዓ.ም.

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

